# የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

መጋቢት 2009

በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በኮርፖሬት ኮሙኒዩኬሽን ዳይሬክቶሬት የሚዘጋጅ ወራዊ ዜና መጽሄት


## የመላው አፍሪካ ቆዳ ንግድ ትርዒት ለ9ኛ ጊዜ ተካሄደ





የመላው አፍሪካ የቆዳ ንግድ ትርዒት በኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪዎች ማህበር አዘጋጅነት ለ9ኛ ጊዜ በአዲስ አበባ ሚሊኒያም አዳራሽ ከመጋቢት 8 እስከ 10 2009 ዓ.ም ተካሄደ፡፡ የንግድ ትርዒቱ ዓላማም ሀገሪቱ ከቆዳው ኢንዱስትሪ የሚገባትን ጥቅም ማግኘት እንድትችል የሚረዳ የንግድ ትስስር መድረክ ለመፍጠር ሲሆን በንግድ ትርዒቱም ላይ ከአውሮፓ፣ ከአሜሪካ ከኤስያ እና ከአፍሪካ ሀገራት የተውጣጡ 150 ሐገራት ተሳትፈዋል፡፡

የቆዳ ንግድ ትርዒቱን በይፋ የከፈቱት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ዴኤታ ክቡር አቶ ቦጋለ ፈለቀ እንደገለፁት እሴት የተጨመረባቸው የቆዳ ውጤቶችን ብቻ ኤክስፖርት እንዲደረግ ያደረግነው ድጋፍ ዛሬ የቆዳው ዘርፍ ለደረሰበት ዕድገት ትልቅ አስተዋፅዎ ማድረጉን ገልፀዋል፡፡ በመቀጠልም በኤሊኮ ዲዛይን የተደረጉ የሴት እና የወንድ የቆዳ አልባሳቶች በኤም ቲ ኤቨንት ፕሮቫይደር አማካኝነት በፋሽን ሾው መልክ ለታዳሚዎች እይታ ብቅተዋል፡፡

የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ትርኢቱን ስፖንሰር ከማድረግ ባሻገር እንደ ተሳታፊ ተቋም የኢጣሊያን ሞዴል ያለቀለት ጫማን፣ ቆዳ ያልሆኑ ምርቶችን (ጫማ እና ቦርሳ)፣ ሌዘር ቦርድ፣ፋት ሊኩዌር፣የሚታጠብ ቆዳ፣ የአዞ ቆዳ፣በክሮም ታንኒንግ ቴክኖሎጂ ከውህአልባ ዌትብሉ የተሰሩ የተለያዩ ቆዳዎች፣ በከፍተኛ ቴክኖሎጂ የተዘጋጁ የተለያዩ ቆዳዎች እንዲሁም ከተለያዩ አይነት የህትመት ውጤቶች ጋር በማቀናጀት ለእይታ አቅርቧል፡፡



በኢንስቲትዩቱ በኩል ለዕይታ ቀርበው በንግድ ትርዒቱ ታዳሚዎች ዘንድ ትኩረት ከሳቡት የምርምር እና ምርት ማልማት ስራዎች መካከል በአዞ እና በዓሳ ቆዳ ተሰርተው የቀረቡ ቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች ይገኙበታል፡፡

በሌላ በኩል በንግድ ትርዒቱ ሁለተኛ ቀን በጫማ እና የቆዳ ምርቶች ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀይለኪሮስ ደበሳይ አማካኝነት የኢንቨስትመንት ፎረም የተካሄደ ሲሆን በፎረሙ ላይም አቶ ሀይለኪሮስ በኢትዮጲ የቆዳ ዘርፍ ኢንቨስት የማድረግ አስፈላጊነት( why to invest in ETHIOPIAN Leather sector) በሚል ርዕስ ገለፃ ካደረጉ በኋላ በድረ-ገፅ አማካኝነት ስለሚደረግ ግብይት እና በትምህርት እና ስልጠና አሰጣጥ እንዲሁም በሌሎች መሰል ኢንስቲትዩቱ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ዙሪያ ሀሳቦች ተነስተው ምላሽ ተሰቶባቸዋል፡፡ የንግድ ትርዒቱም ዕሁድ መጋቢት 10 ቀን 2009 ዓ.ም ተጠናቋል፡፡


**ዋና አዘጋጅ**

አቶ ብርሀኑ ሰርጄቦ

**አዘጋጆች**

ብሩክ ጥላሁን

ታድሎ ንጋት

ዓለምነህ ቸርነት

**ዲዛይን**

ዓለምነህ ቸርነት

**ፎቶግራፍ**

ሙላቱ ዘነበ



**አድራሻ**

**የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት**

Tel: +251-11-4-39 17 00

+251-11-4-39 16 82

+ 251-11-4-39 66 4

Fax: +251-11-4- 39 22 59

P. O. Box: 24692 code 1000 A/A

E-mail: contact@elidi.org

Web: www.elidi.org

# የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

መጋቢት 2009

## የቆዳ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ ሁለተኛው የህዝብ ክንፍ የምክክር መድረክ



የካቲት 25/2009 አዲስ አበባ፡- የ2009 በጀት ዓመት የሁለተኛው ሩብ ዓመት የቆዳ እና ቆዳ ዉጤቶች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ የህዝብ ክንፍ የምክክር መድረክ የካቲት 25/2009 ዓ.ም በኔክሰስ ሆቴል አዳራሽ ተካሄደ፡፡

በምክክር መድረኩ ላይ የኢፌዲሪ ኢንዱስትሪ ሚኒስትር ክቡር አቶ አህመድ አብተው፣ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የጨርቃጨርቅና ቆዳ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ክቡር አቶ ቦጋለ ፈለቀ፣ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ወንዱ ለገሠ፣ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች፣ የንዑስ ዘርፉ ማኅበራት ፕሬዚዳንቶች፣ የፋብሪካ ባለቤቶችና የሥራ መሪዎች፣ አገልግሎት ሰጭ የመንግስት ተቋማት፣ የዩኒቨርሲቲ፣ የክልል ቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ ተወካዮች፣ ሚዲያዎችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች የተገኙ ሲሆን የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢነስቲትዩት እቅድና መረጃ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ተስፋዬ ብርሃኑ በመጀመሪያው የህዝብ ክንፍ የመድረክ ውይይት ወቅት ለዘርፉ እድገት እንቅፋት ናቸው ተብለው የነበሩ ዋናዋና ነጥቦች በአብዛኛው የማስተካከያ እርምጃ እየተወሰደባቸው መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በዚህም መሰረት በመጀመሪያው የህዝብ ክንፍ መድረክ ለዘርፉ እድገት እንደመሰናክል ከተነሱት ነጥቦች መካከል የአገር ውስጥ ቆዳ አምራችና ላኪ ኩባንያዎች የስራ ሁኔታ ከጊዜ ወደጊዜ እየተዳከመ መምጣት፣ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ጥራትና ብክነት ጉዳይ እንዲሁም ከገበያ ጋር የተያያዙ ችግሮች እንደሚገኙበት አስታውሰው ከአገር ውስጥ ቆዳ አምራችና ላኪ ኩባንያዎች አቅም እየተዳከመ መምጣት ጋር በተያያዘ ዋና ዋና ችግሮችን፣ የችግሮችን መንስኤዎችና ደረጃዎች በማጤንና በመመርመር መፍትሄ የማስቀመጥ ስራ ለመስራት ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ያካተተ ኮሚቴ ተቋቁሞ እንዲሰራ ተደርጓል ብለዋል፡፡ከጥሬ ቆዳ ብክነትና ጥራት ችግር ጋር በተያያዘም ችግሮችን ለመፍታት በተከናወነ ስራ ከዚህ በፊት የነበረው የጥሬ ቆዳ አዋጅ እንደአንድ መሰረታዊ የችግር መንስኤ ሆኖ በመገኘቱ አዋጁ ተስተካክሎ ለአስተያየት ወደሚመለከተው አካል እንደተላከም አቶ ተስፋየ ገልጸዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ አቶ ተስፋየ ብርሀኑ የ2009 የስድት ወር የኤክስፖርት አፈጻጸም ለተሳታፊዎች በዝርዝር ገለጻ ያደረጉ ሲሆን ካቀረቡት ገለጻ መረዳት እንደተቻለው በበጀት አመቱ ሁለተኛ ሩብ ዓመት 55.5 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ ከእቅዱ የ42.9 በመቶ ቅናሽ በማሳየት 31.7 ሚሊዮን ዶላር ብቻ መገኘቱ ተመላክቷል፡፡

የተገኘው ገቢ ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በአለቀለቀት ቆዳ ኤክስፖርት የ5.85 እና በቆዳ ጓንት፣ አልባሳትና እቃዎች ደግሞ የ0.65 ሚሊዮን ዶላር ቅናሽ አሳይቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ 17 ያህል ያለቀለት ቆዳ አምራች ድርጅቶች ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በዚህኛው ሩብ ዓመት የ9.48 ሚሊዮን ዶላር ያህል ቅናሽ ሲያሳዩ በአንጻሩ ሦስት የጫማ አምራችና ላኪ ፋብሪካዎች የ2.37 ሚሊዮን ጭማሪ አስመዝግበዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ንዑስ ዘርፉን ለማዘመንና ከዘርፉ የሚጠበቀውን ተጠቃሚነት ለማሳደግ ከሚረባረቡ አካላት መካከል የሚጠቀሱት የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪዎች ማህበርና የጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢዎች ማህበር የግማሽ ዓመት አፈጻጸም ሪፖርቶቻቸውን አቅርበዋል፡፡ የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪዎች ማህበር በኤክስፖርት ፕሮሞሽንና በግብዓት አቅርቦት ረገድ በርካታ ስራዎች ማከናወኑን በሪፖርቱ ገልጿል፡፡

የውይይቱ ተሳታፊ የነበሩ ባለሀብቶች በበኩላቸው አሁን እየታየ ላለው የኤክስፖርት መሸቀልቀል የገበያ መዳረሻ፣ የምርት ጥራት፣ የፋይናንስ፣ የመመረቻ ቦታ እጥረት እንዲሁም የጉሙሩክ የባውቸር አሰራር ስርዓትና ሌሎች የተንዛዙ ሂደቶች ለኤክስፖርት ስራቸው ማነቆ እንደሆኑባቸው ጠቅሰው ዘርፉ በተፈለገው መልኩ እንዲያድግ ለማድረግ መንግስት ከላይ የተጠቀሱትን ጨምሮ ያሉበትን ችግሮች በአፋጣኝ እንዲፈታ አሳስበዋል፡፡



በምክክር መድረኩ ላይ የተገኙት የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ወንዱ ለገሰ አገራችን ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለምታደርገው የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ሂደት ከፍተኛ ሚና ካላቸውና ግንባር ቀደም ትኩረት ከተሰጣቸው መስኮች መካከል የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ አንዱ መሆኑን አስታውሰው በ1ኛው ዕትዕ እቅድ ዘመን ዘርፉ በፍጥነት እንዲያድግና በዓለም ዙሪያ ተወዳዳሪ እንዲሆን የሚያስችሉ በርካታ ስራዎች መከናወናቸውን አስረድተዋል፡፡

ከተከናወኑ አበይት ተግባራት መካከልም የአቅም ግንባታ፤ የቴክኖሎጅ ሽግግር፤ በምርቶች ላይ እሴት በመጨመር ወደዓለም አቀፍ ገበያ ማቅረብና ሌሎች ንዑስ ዘርፉን ትራንስፎርም ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራት እንደተከወኑ ተናግረዋል፡፡

የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ወንዱ ለገሰ በገለጻቸው ወቅት እንዳብራሩት እንደአገር ወደዕሴት ጭማሪ በመሸጋገር ትልልቅ ፋብሪካዎች መከፈት መጀመራቸው የኢትዮጵያ ቆዳ ቴክኖሎጂንና አቅምን አሟጦ በመጠቀም ከተሰራበት የተሻለ ዋጋ እንደሚያወጣ ማሳያ መሆናቸውን ጠቁመው የዓለም ገበያን ሰብሮ ለመግባት ተቋማዊ አቅምን መገንባት፣ የቴክኖሎጂ ደረጃን ማሻሻል

እና የሰው ሀይል ማደራጀት አስፈላጊ መስፈርቶቸ በመሆናቸው  እነዚህን ማሟላት ከአብዛኛዎቹ ፋብሪካዎች እንደሚጠበቅ አሳስበዋል፡፡የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ወንዱ ለገሰ  በገለጻቸው ማጠቃለያ ተጨማሪ እሴት ያላቸውን ምርቶች የማስቀጠልና የመደገፍ ሂደት በኢንስቲትዩቱ በኩል ቀጣይነት እንደሚኖረው ለባለሀብቶችና ባለድርሻ አካላት ተናግረዋል፡፡

በውይይቱ ላይ የተገኙት  የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር  ክቡር አቶ አህመድ አብተው ለተነሱ ጥያቄዎች ምላሽ የሰጡ ሲሆን ለኤክስፖርት መቀነስ ምክንያት ናቸው ተብለው በተሳታፊዎች በኩል የተነሱት ችግሮች ሙሉ በሙሉ የሉም ባይባልም አሉ የተባሉ ውስብስብ የአሰራር ሥርዓቶችን ማስተካከል ከመንግሥት የሚጠበቅ  መሆኑን አመላክተው በዘርፉ የተሰማሩ በርካታ አገርበቀል ፋብሪካዎች ተወዳዳሪ ሆነው ለመቀጠል ግን ያላቸውን ቴክኖሎጂ የማስፈጸም ዓቅምና የክህሎት ክፍተት ማሳደግ እንደሚጠበቅባቸው አሳስበዋል፡፡

እንዲሁም ሚኒስትሩ ንዑስ ዘርፉ አገሪቱ ላቀደችው ዕትዕ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት በመሆኑና መንግስት ተጨማሪ ዕሴት ምርቶችን ለማሳደግ ባለው ፍላጎት  ለንዑስ ዘርፉ የሚደረገው ድጋፍ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልና መንግሥት ባለው ቁርጠኝነት በቀጣዩ የቴክኖሎጂ ሽግግር ዘመቻ እንደሚያደርግ አስገንዝበዋል፡፡

## የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ከህንድ በመጣ ከፍተኛ ኤክስፐርት ለኤክስፖርት ተኮር ፋብረካ ባለቤቶችና ከፍተኛ ባለሙያዎች በቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች መሰረታዊ የቅርጽና ዲዛይን አሰራር ላይ ሥልጠና ሰጠ

በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የቆዳ አልባሳትና እቃዎች ማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት በቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች መሰረታዊ ቅርጽና ዲዛይን(basic pattern and design) ኤክስፖርት ተኮር ለሆኑ 17  ፋብሪካዎች ባለቤቶችና ከፍተኛ ባለሙያዎች ከህንድ በመጣ አንድ ከፍተኛ ኤክስፐርት የ10 ቀን ሥልጠና ከየካቲት 13 እስከ 24 2009 ሠጠ፡፡ የሥልጠናው ዓላማ  የቆዳ አልባሳት አምራች ኩባንያዎች   ዓለምአቀፍ የሆኑ የኤክስፖርት ማሟያዎችን በሚገባ እንዲረዱና የምርታቸውን ብቃት በዛ ደረጃ እንዲያሳድጉ ለማስቻል መሆኑን በቆዳ አላባሳትና እቃዎች ማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት የሥልጠናው አስተባባሪና የኢንስቲትዩቱ አሰልጠኝ የሆኑት  አቶ ግርማ  ደንጎራው ገልጸዋል፡፡



ሥልጠናው በንድፈ ሀሳብ፤ በተግባራዊ ልምምድና ሰርቶ ማሳያ  ላይ መሰረት አድርጎ የተሰጠ ሲሆን  በዚህም መሰረት ሰልጠኞች  በሥልጠናው  ያገኙትን ዕውቀት መቅሰማቸውን ለመለካት ናሙና ቅርጽና ዲዛይን ሰርተው እንዲያሳዩ በማድረግ ውጤታቸው ተገምግሞ በቂ ክህሎት እንዳገኙና የተሻለ አቅም እንደገነቡ የሥልጠናው አስተባባሪና የኢንስቲትዩቱ አሰልጠኝ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ሠልጠኞች በበኩላቸው በቂ ዕውቀትና ክህሎት  ከሥልጠናው እንደጨብጡ



የተናገሩ ሲሆን በዚህ ስልጠና ተሳታፊ ከሆኑት ፋብሪካዎች መካከል በቆዳው ዘርፍ አንጋፋ እድሜ ያስቆጠረው ኤሊኮ ዩኒቨርሳል የቆዳ ዕቃዎች ፋብሪካ አንዱ ተጠቃሽ ነው፡፡ የካምፓኒው የዲዛይንና ምርት አገልግሎት ክፍል ሀላፊ የሆኑት አቶ ብስራት አስፋው  ኤሊኮ ቀደም ሲል ጀምሮ የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎችን ለኮሪያ፣ጀርመን፣ አሜሪካ፣ ሲዊዲን ላሉት አገራት እየላከ የሚገኝ ቀደምት ፋብሪካ መሆኑን አመልክተው ከኢንስቲትዩቱ  በሥልጠና፣ በማማከር አገልግሎትና በማሽነሪ ጥገና ትልቅ የሚባል ድጋፍ እያገኙ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ አቶ ብስራት ከሥልጠናው ጋር ሊያየዘው እንደተናገሩት ሥልጠናው ከዚህ በፊት ከተሰጡት በዓይነቱ ልዩ መሆኑን ጠቁመው በተለይም አሰልጣኙ በዘርፉ  ከፍተኛ ዕውቀትና ልምድ ያካበቱ በመሆናቸው ዓለምአቀፍ የቴክኒካዊ ስታንዳርድ አሰራርን እንድንጨብጥ አስችሎናል ብለዋል፡፡ አቶ ብሥራት ከዚህ ቀደም በኢኒስቲትዩቱ በቆዳ አላባሳትና ዕቃዎች ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት የሶስት ወር ሥልጠና በኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች ማግኘታቸውን አስታውሰው ይኼም ሰራተኞቻቸው  በንዑስ ዘርፉ ቴክኖሎጂ እራሳቸውን እንዲለወጡ እንደረዳቸውና በፋብሪካቸው  አሰራር ተጨባጭ የሚባል ለውጥ እንዳስገኘላቸው  አመላክተው አሁን ያገኙት ሥልጠና ደግሞ የበለጠ እንዲሻሻሉ እንደሚያግዛቸውና ለዚህም ያገኙትን ዕውቀትና ክህሎት ለፋብሪካቸው መካከለኛ ደረጃ ባለሙያዎች ለማከፈል ዝግጅት እንዳላቸው አስረድተዋል፡፡

ከህንድ ኮልካታ የፉትዊር ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የመጡት፣ በዘርፉ ለ26 ዓመት የካበተ ልምድ ያላቸውና በመላው ዓለም በመንቀሳቀስ በቆዳው ዘርፍ የዲዛይንና ቅርጽ አሰራር ሥልጠና በመስጠት ላይ የሚገኙት ሚስተር አብጂት ሬይ እንደሚሉት በበርካታ የዓለማችን ክፍል ኢትዮጲያን ጨምሮ በቆዳ አልባሳት ዘርፍ  በቅርጽና ዲዛይን አሰራር እንዲሁም በማቴሪያል መረጣ ገበያው የሚፈልገውን ለመስራት ትልቅ ክፍተት መኖሩን አመላክተው ይህ ሥልጠና ይኼንን ክፍተት ለመሙላት እንዲያስችል ታስቦ የፋብሪካዎች ከፍተኛ ባለሙያዎች ብቃትን ለማሻሻል መሰጠቱንና ሥልጠናውም የተሸለ ክህሎት እንዲቀስሙ ያስቻለና ለካምፓኒያቸው ምርት መሻሻል የበኩሉን አስተዋጽኦ የሚያበረክት በመሆኑ በሥልጠናው  አቀባበል ደስታ እንደተሰማቸው ገልጸዋል፡፡

ሚስተር አብጂት የቆዳው ዘርፍ በአገራችን ያለበትን ሁኔታ ሲያብራሩ "በኢትዮጲያ የጥሬ ቆዳ ግብዓት በበቂ ሁኔታ በመኖሩና የቆዳ ኢንዱስትሪዎች በብዛት እያቆጠቆጡ የመጡበት ሁኔታ ስላለ በዲዛይንና ፕሮዳክሽን ሥራ የተሻለ ለመስራት መልካም አጋጣሚ እንደሚፈጥር ተናግረዋለ፡፡

ሥልጠናውን ያገኙት የኤክስፖርት ተኮር ፋብሪካዎች  ባለቤቶችና ባለሙያዎች በሥልጠናው ሂደት ከቆዳ ኢንደስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የተሟላ የሥልጠና ማቴሪያሎችና ፋሲሊቲዎች  የቀረበላቸው ሲሆን በቀጣይም ግንኙነታቸውን ከኢንስቲትዩቱ ጋር በማጠናከር የተሻለ ኤክስፖርት አፈጻጸም እንዲኖራቸው የክህሎት ዓቅማቸውን ከማሳደግ አንጻር በኢኒስቲትዩቱ በቂ እገዛ እንደሚደረግላቸው  የኢንስቲትዩቱ የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች አሠልጠኝ አቶ ግርማÀ ደንጎራው ገልጸዋል፡፡ በሥልጠናው መጨረሻ  በኢኒስቲትዩቱ የቆዳ አላባሳትና እቃዎች ማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት አማካኝነት ለሰልጣኞች የምስክር ወረቀት ተሰጥቷል፡፡

## የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ከቆዳው ዘርፍ ለተወጣጡ ባለሙያዎች በላብራቶሪ አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚያተኩር ስልጠና ሰጠ



**አዲስ አበባ፡-**የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ከተለያዩ የቆዳ ፋብሪካዎች ለተወጣጡ ባለሙያዎች በላብራቶሪ አልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ያተኮረ የ 4 ቀን ስልጠና ከመጋቢት 4 እስከ 7 2009 ዓ.ም ሰጠ፡፡ ስልጠናው የትምርትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት በተለያዩ የጫማና የቆዳ ፋብሪካዎች የሚመረቱ ምርቶች የጥራት ሁኔታ ጋር በተያያዘ ባደረገው ጥናት የታዩ ክፍተቶችን ለመሙላት ታስቦ እንደተዘጋጀ ስልጠናውን ከሰጡት መካከል በፍተሻና ምርምር ለብራቶሪ ሲኒየር የፊዚካልና መካኒካል ፍተሻ ተመራማሪ አቶ ፀጋአብ በቀለ ተናግረዋል፡፡

ስልጠናው ዘርፉን አስመልክቶ በዓለም ዙሪያ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ከማስገንዘቡም ባሻገር የሚያምርቷቸውን ምርቶች ጥራት በማስፈተሽና ጥራታቸውን በማረጋገጥ በዓለም የዘርፉ ገበያ ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ እንደሚያስችልም አቶ ፀጋአብ ገልጸዋል፡፡

ስልጠናው ባለሙያዎች የምርት ጥራት ምንነትን በበቂ ሁኔታ እንዲገነዘቡ፣ምርቶቻቸውን በጥራት በማምረት፣በማስፈተሽና ጥራታቸውን በማረጋገጥ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ የሆኑ ምርቶችን ይዘው እንዲቀርቡና ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሬ እንዲያገኙ ያስችላል ተብሎ እንደሚጠበቅ የተናገሩት አቶ ፀጋአብ በገዥዎች በኩልም ለሚከፍሉት ክፍያ ተገቢነት የሚያረጋግጥና በአምራቾች ዘንድ ተአማኒነትን እንደሚያስገኝ ጨምረው ተናግረዋል፡፡

ሰልጣኞች በበኩላቸው ከዚህ በፊት የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ ስርዓትን ጨምሮ በሌሎች ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ስልጠና የወሰዱ መሆናቸውን አስታውሰው ይሄኛው ስልጠና ከዚህ በፊት ከወሰዱት ስልጠና አንድ ደረጃ ከፍ በማድረግ የሚያመርቷቸውን ምርቶች የጥራት ምንነት በፍተሻ በማረጋገጥ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ የሆነ ምርት ይዘው ለመቅረብ እንደሚያግዛቸው ተናግረዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ሠልጣኞች በየፋብሪካዎቻቸው ላብራቶሪ እንዲያቋቁሙ እንደሚያግዛቸውና የሚያቋቁሙት ላብራቶሪ እንዴት እውቅና ማግኘት እንዳለበትና የመሳሰለሉትን ስራዎች ለማከናወን ሥልጠናው የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ እንደሆነ ከአዲስ አበባ የቆዳ ፋብሪካ የመጡት አቶ ተስፋየ አያሌው ተናግረዋል፡፡

በመጨረሻም ጥራት የአንድ ጊዜ ስራ ብቻ ሳይሆን ቀጣይነት ያለው መሆኑን ያስገነዘቡት አቶ ፀጋአብ ፋብሪካዎች ይህንን በመገንዘብ በየጊዜው የሚያደርጉትን የጥራት ቁጥጥር በአግባቡ እንዲይዙ፣ እንዲገመግሙና ግምገማውን መሠረት ያደረገ የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምርቶቻቸውን ቀጣይነት ባለው መልኩ በማሻሻል ለዓለም ገበያ ማቅረብ አለባቸው ሲሉ አሳስበዋል፡፡





# የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ትምህርታዊ ጉብኝት አካሄዱ



ጥር 29/2008 ዓ.ም አዲስ አበባ ፡- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ 3ኛ ዓመት የኢንዱስትሪያል የኬሚስትሪ ተማሪዎች በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ትምህርታዊ ጉብኝት አካሄዱ፡፡

ተማሪዎች በጉብኝታቸው ወቅት የኢንስቲትዩቱን የምርምርና የፍተሻ ክፍሎች፡የሞዴል ታነሪና የምርት ሂደት፡እንዲሁም የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ትሪትመንት ፕላንትን ተመልክተዋል፡፡

ተማሪዎቹ በጉብኝቱ ወቅት የተመለከቱት የሞዴል ፋብሪካ እንቅስቃሴ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ የተማሩትን ጽንሰ ሃሳብ ከተግባር ጋር ለማስተሳሰር የሚያስችል ከፍተኛ ግንዛቤ እንደፈጠረላቸውም ተናግረዋል፡፡

በጉብኝቱ የተገኙት የዩኒቨርስቲው  ኢንስትራክተር ከተማው ሳለልኝ በበኩላቸው የተደረገላቸው አቀባበል እንዳሰደሳታቸው ገልጸው የጉብኝት ሂደቱ የተማሪዎችን ቁጥር ያገናዘበ በመሆኑ ተማሪዎቹ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ የተማሩትን ጽንሰ ሃሳብ ወደተግባር ለመተርጎም የሚያስችል በቂ ግንዛቤ እንደሚፈጥርላቸው ተናግረዋል፡፡

የጉብኝቱ ዓላማ ጽንሰ ሀሳብን ከተግባራዊ እንቅስቃሴ ጋር ማስተሳሰር መሆኑን ያስታወሱት ኢንስትራክተሩ ከዓላማ አንጻር ሲታይ የተከናወነው ትምህርታዊ ጉብኝት ውጤታማ እንደነበር ገልጸዋል፡፡በዘርፉ በኩል እየታየ ያለውን ብቁና ጥራት ያለው የሰው ኃይል እጥረት ለመቅረፍ አገሪቱ በተለያዩ ተቋማት በኩል እያደረገች ያለውን ጥረት በማገዙ ረገድ ኢንስቲትዩቱ እያበረከተ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ ለወደፊቱም መሰል ድጋፉን አጠናክሮ እንዲቀጥል ሲሉ ኢንስትራክተሩ አሳስበዋል፡፡





**ተማሪዎች በጉብኝት ወቅት**

## የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በISO 2009፡2008 የጥራት ስራ አመራር ሥርዓት ዙሪያ ለሰራተኞቹ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ሰጠ



**መጋቢት 12/2009 ዓ.ም አዲስ አበባ:** የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዮት በISO 2009፡2008 የጥራት ሰራ አመራር ሰርዓት ዙሪያ ለሰራተኞቹ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ሰጠ፡፡ ስልጠናው በሁለት ዙር ለአንድ ቀን የተሰጠ ሲሆን በጥራት ስራ አመራር ስርዓት ጽንሰ-ሀሳብ፣በመርሆዎችና ጠቀሜታዎች ፣በመስፈርቶችና አፈጻጸማቸው፣በሀብት አስተዳደር፣ በጥራት ምዘና አፈጻጸም ክትትልና ማሻሻያ እንዲሁም በሌሎች ርዕስ ጉዳዮች ዙሪያ ያተኮረ እንደነበር ከተገኘወ መረጃ ማወቅ ተችሏል፡፡

የISO 2009-2008 የጥራት ስራ አመራር ሰርዓትን በአንድ ተቋም ውስጥ መተግበር ውስጣዊና ውጫዊ የሆኑ ጠቀሜታዎች እንዳሉት የተናገሩት በፍተሻና ምርምር ላብራቶሪ ሲኒየር የፊዚካልና መካኒካል ፍተሻ ተመራማሪ አቶ ፀጋ አብ በቀለ የድርጅቱን ዓላማ በግልጽ ለማሳወቅ፣ ብቁ ማኔጅመንት ለመፍጠር፣የጥራት ችግር መንስኤዎችን ለመለየት፣ሀብትን በአግባቡ ለመጠቀም፣የስራ ግንኙነትን ለማሻሻል ከውስጣዊ እንዲሁም በገበያ ብቁ ተወዳዳሪ ለመሆን፣የደንበኞችን ፍላጐት ለማርካት፣ደንበኛ በሚያገኘው አገልግሎት እምነት እንደኖረው ለማድረግና የመሳሰሉት ደግሞ ከውጫዊ ጠቀሜታዎች ለዓብነት እንደሚጠቀሱ ለሰልጣኞች አብራርተዋል፡፡

የጥራት አስተዳደር ሰርዓት መስፈርቶችን እንደየድርጅቱ ዓይነትና ተጨባጭ ሁኔታ በአግባቡ መተግበር አስፈላጊውን ውጤት ለማስመዝገብ ያስችላል ያሉት አቶ ፀጋአብ የሚዘረጋው የጥራት አሰተዳደር ስርዓት የድርጅቱን ደንበኞች ማዕከል ያደረገና ፍላጐታቸውን በተሟላ መልኩ የሚያረጋግጥ ሊሆን እንደሚገባም ለሰልጣኞች አስረድተዋል፡፡

አንድ ድርጅት የደንበኞችን እርካታ በሚፈልገው መልኩ ለማረጋገጥ በጥራት ስራ አመራር መሳፍርቶች መሠረት የቁጥጥር ስርዓት አጣምሮ ሊዘረጋ ይችላል ያሉት አሰልጣኙ ይሁን እንጂ የተዘረጋው ስርዓት ውጤታማ መሆንና አለመሆኑን የውስጥ ኦዲት በማድረግ በመቆጣጠርና በመለካት ማረጋገጥ ይገባል ብለዋል፡፡



ስልጠኞች በበኩላቸው የጥራት ሰራ አመራር ስርዓት ድርጅቶችን ያለምንም እንከን ለመምረጥ፣ የሰው ኃይልን፣የማምረቻና አገልግሎት መስጫ መሳሪያዎችን፣ማንኛውንም ስራ ለማከናወን የሚያስችሉ ዝርዝር መመሪያወችንና የመሳሰሉትን ያካተተ በመሆኑ ድርጅቶች ተጠቃሚን ሊያረካ የሚችል ምርትና አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስችል መሆኑን ተገንዝበናል ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

በመጨረሻም ከተሳታፊዎች የተለያዩ ጥያቄዎች ተነስተው በአሰልጣኙ በኩል ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

**አስተያየታችሁን በኢሜል አድራሻችን**

**contact@elidi.org ብላችሁ**

**ብትልኩልን በደስታ እንቀበላለን**